# የአክራሪው ዳያስፖራ ጩኸትና ዴሞክራሲን የማዘግየት ሚናው

**ተወልደብርሃን ክፍሌ**

ዴሞክራሲ እንደማናቸውም ስርዓቶች(ስነ-ህይወታዊ፣ማኀበራዊ፣ኢኮኖሚያዊ ወ.ዘ.ተ) እንዲበቅል እንዲፋፋና በልፅገ አዎንታዊ ተፅዕኖ እንዲፈጥር ወሳኝ የሆኑ መሰረታዊ መደላድሎችን ይፈልጋል፡፡ግብአቶቹም የህዝቡ ታሪክ፣ባህል፣ ስነ-ልቦናና ንቃተ-ህሊና፣የኢኮኖሚ ሁኔታና ተጠቃሚነት ፣የሀገሪቱን ህገ-መንግስትና ከዚሁ የሚመነጩ ህጎች፣ምርጫ፣ሐሳብን በነፃነት የመግለፅና ተያያዥነት ያላቸው ተቋማት፣የስልጣን አካላትና የተጠያቂነት ስርዓት፣ እንዲሁም ለዚሁ ጥበቃ የቆሙ ተቋማትን ወ.ዘ.ተ. ይጨምራል፡፡ በዚህ ፅሑፍ የአክራሪው ዳያስፖራ ጩኸትና ፖለቲካዊ አጉራ-ዘለልነት እላይ በተጠቀሱ ግብአቶች ላይ በአንድ ወይም በሌላ መልኩ በሚፈጥረው ተፅዕኖ የምንመኘውን ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እንዴት እንደሚያዘገይብን ለማሳየት ይሞከራል፡፡ «ማዘግየት» የሚለውን ቃል የተመረጠበት ምክንያት ደግሞ ይህ ሃይል ሊያደርስ የሚችለውን የመጨረሻ ጉዳት ይኸው በመሆኑ ነው፡፡

አክራሪው ሐይል የሚንቀሳቀስበት አኳሀን ክፍት-ቀለበት የሚሉት ዓይነት ነው፡፡ ይጮሀል እንጂ የጩኸቱን ውጤት በራሱና በሌሎች ወገኖች ላይ የሚፈጥረው በጎም ይሁን መጥፎ ሁኔታ ለመገምገም የተዘጋጀ አይደለም፡፡ብቻ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ይጮሀል፡፡ አንዱን ጥሎ ሌላውን ያነሳል፡፡ ስለዚህም ስለዚያም ይጮሃል፡፡ የጩኸት ቡድኑ ራሱ ወይም በሳተላይት የሚቆጣጠረው ሌላ ቡድን በትረ-መንግስቱ ካልጨበጠ ሀገሪቱ ገደል እንደምትገባ፤በዘር፣ በሀይማኖት፣ ተከፋፍላ ብትንተንዋ እንደምትወጣ፤በሙስና ተመዝብራ አጥንቷ ብቻ እንደሚቀር፣ለውጭ ሐይሎች ተላልፋ እንደምትሸጥ እንደዚሁም እግዚአብሔር በዓለም ላይ ያለውን መከራ ሁሉ አክብዶ እንደሚጭናት ይተነብያል፡፡ ያስተነብያል፡፡ አዋጅ ያስነግራል፡፡ በክፍት ቀለበት «ሞድ» የሚሰሩ ስርዓቶች ከስህተታቸው የሚማሩበት ባህሪያዊ አቅም የላቸውም፡፡ ብቸኛ ተስፋቸው ከውጭ የሚቸራቸው ምክርና ተግሳፅ ላይ የተንጠለጠለ ሲሆን መጮህን እንጂ «መስማት የተሳናቸው» ሆነው የተገኙ እንደሆን አበሳቸው የበረታ ያደርገዋል፡፡ የነዚህ አክራሪ ሐይሎች ችግርም ይኸው ነው፤ ዲሞክራሲን ይኖሩታል እንጂ አያውቁትም፡፡ የሌላውን ሰው ሐሳብ ሚዛን መስጠት እንደ መብላትና መጠጣት የተለመደ በሆነባቸው ዓለማት ውስጥ እየኖሩ ጩኸታቸውን ብቻ እንድናደምጥ ይሻሉ፡፡ ለየት ያለ ሐሳብ የሚያራምድ ካለማ ወዮለት፡፡ የስድብ ናዳ ይለቀቅበታል፡፡ የሚያቀርባቸው ምርቶችና አገለግሎቶች ካሉ ደግሞ እንደተባበሩት መንግስታት በጋራ ወይም በተናጠል ማዕቀብ ይጣልበታል፡፡ የሚዝናናበት ሬስቶረንት፣የሚሳፈርበት አይሮፕላን ይወሰንበታል፡፡

ይህ ሐይል ነገረ-ስራው በዚህ አያበቃም:: ካለበት ሆኖ የትጥቅ ትግል ያውጃል:: ቀድመው ካወጁትም ቃልኪዳኑ ያድሳል:: ትጥቅ ትግሉ ከበረሀ እንዲሁም እንደሁኔታው ከከተማ የሚሰነዘር ሊሆን ይችላል:: በስልጣን ላይ ያለውን መንግስት በከፋፋይነት በወነጀለበት አፉ የለየላቸውና እንገነጠላለን የሚሉትን ሐይሎች ጋር ተሰልፎ መፈክር ይለፍፍበታል:: የሌሉ ታሪኮች ይፈጥራል:: ፍንጭ ካገኘማ ጭራና ቀንድ ያበቅልበታል:: የጥፍር ክርካሚ ያገኘ እንደሆን እጅ መቆረጡን ለ«ሰብአዊ መብት ተሟጋቾች» ያቀብላል:: በዚሁም የሃገሪቱን ስም ደጋግሞ ያነሳል:: ይወቅሳል:: የሃገር ውስጥ ወኪሎቹም ጭኸቱን ያደምቃሉ:: በአራቱም ማዕዘናት ዘመቻ መከፈቱን «ታማኝ ምንጮቻቸውን» በመጥቀስ ይዘግባሉ:: ምን ይሄ ብቻ መስከረም ሲጠባ ምልአተ-ህዝቡ አዲሳባን ጎረፍ ሆኖ እንደሚጠርጋት ልብ ያለው ልብ እንዲል የነብዩ ምክራቸውን ይለግሳሉ:: ዕፈው ሲያበቁ ደግሞ ቀሪ ጊዜያቸውን ይፖተልኩበታል:: ከዚህ ወይም ከዚያኛው ፓርቲ ጋር ሆነው የጥቃት ስትራትጂ ያወጡበታል:: ሃይ ባይ ህግ-አስከባሪ ቢገኝ ዕድሜ ለአክራሪው ሐይል ይጮህለታል:: የዚያ ሰው ስሙ ካፋቸው ፎቶው ከደረታቸው አይጠፋም:: «የህሊና እስረኛ» ተብሎ ሻማ ይበራለታል:: ስለ «በነፃ ሐሳብ» መግለፅ ይሰበካል:: «በህይወት ያልኖረው ነፃ ፕሬስ» መሞቱን ይነገርለታል:: ከዚህ ጎን ለጎን «አፋኝ» አዋጆች ስም ይጠቀሳል:: የፀረ-ሽብር፤ የሲቪክና የበጎ አድራጎት ድርጅቶች አዋጆች ይበጠለጠላሉ:: አዋጆቹ በትክክል ይነበቡ አይነበቡ የሚጠይቅ ካለ እሱ የለየለት እብድ መሆን አለበት::የሽብር አዋጁ ይህን ሀይል ከመሸገበት ሃገር «የተኮረጀ» መሆኑን ፤ሌላኛው አዋጅም የፖለቲካና የምግባረ-ሰናይ ሚና ለመለየት በዚሁም የፖለቲካ ተሳትፎ የዜጎች እንጂ የባለገንዘብ መጫወቻ ሜዳ መሆን እንደማይገባው ቢነገረውም ለመጮኽ እንጂ ለመስማት አልታደልምና ሊሰማ አልቻለም:: ረጃጅም እጆች ይገኙበታል በተባለ ቦታ ሁሉ ተገኝቶ እንደጮኸ 2005 ዓ/ም ደረስን ::

እግዚአብሔር ምስጋና ይግባውና ለዚህ ሀይል የሚጮህበትን ነገር አሳጥቶት አያውቅም:: «ፈልጉ ታገኛላችሁማል» አይደል ያለው ቅዱሱ መፅሐፍ? እናም የሚጮህበት ጉዳይ መብዛቱ:: ግልገል ጊቤ 3 አንዱ የፊልሚያ ግንባር እንዲሆን ተፈረደበት:: ከቱርካና ሐይቅ ጓደኞችና ከ«አርንጓዴው እንቅስቃሴ» አራማጆች ጋር ጓደኝነት በመፍጠር አረንጓዴውን ልማት ሊያደናቅፍ ቆርጦ ተነሳ:: የኤውሮጳና የሰሜን አሜሪካ ስነ-ምህዳር ጠበብቶችን ተማፀነ:: ሳሊኒን ደግሞ በዚህ ቡድን ጩኸት ምክንያት በተሰነጣጠቀችው ቤተክርስትያን በአንዷ «አባቶች» ውግዝ ከመአርይምስ» አሰኘ፤ አስወገዘ፤ አስረገመ:: ለዚህ ተግባር የሚወል ገንዘብ ያበደረ ተቋምም ሆነ መንግስት ገንዘቡ ጭዳ ያደርገው ዘንድ ፈጣሪውን ለመነ፤ ፀለየ:: በዚሁ ጉዳይ ላይ ሱባኤ እንደተቀመጠ የባሰውን መጣበት:: አባይን:: አዎ አባይን:: ለኢትዮጵያውያን የአባይን ጉዳይ እንደ ግለገል ጊቤው ቀላል እንደማይሆንላቸው በመተማመን የጩኸቱን «ቮልዩም» አስተካከለ:: በአጭርና በመካከለኛ ሞገዶች የተለቀቀው ጩኸት ከሰው ጆሮ አልፎ የግብፅ ፒራሚዶችንም አስበረገገ:: በአብዮት ማዕበል ስትናወጥ የነበረችው ግብፅ ለጊዜው ግራ ገብቷት ዝምታን

በመረጠች ጊዜ የጨኸቱን አቅጣጫ ማስለወጡን ቀጠለ:: እናም እንዲህ አለ:: በኑሮ ውድነት እየተገረፈ ላለ ህዝብ ተጨማሪ «አበሳ» የሚቆጥርበት ፕሮጀክት ከመሆኑም በላይ ለድንበር የቀረበ በመሆኑ ለአደጋ የተጋለጠ ነው አለና አረፈው:: ፕሮጀክቱ የጠነሰሱት አፄ ሃይለስላሴ በመሆናቸው ያሁኑ መንግስት «ከጥሩንባ ነፊነት» የዘለለ ሚና እንደሌለው «በጥናት» ላይ የተመሰረተው ጨኸቱ አስተጋባ:: እዚህም ቢሆን ግለገል ጊቤ ላይ እንዳደረገው ሁሉ የልገሳ እጆች እንዳይዘረጉ፣ ቦንድ  እንዳይገዙ ተማፀነ:: በሀገር ውስጥም መንግስት  ህዝቡን ገንዘብ እንዲለግስና ቦንደ እንዲገዛ «እያስገደደው» እንደሆነ  ከሀገር ውስጥ ወኪሎቹ ጋር ሆነው በአንድ አፍ አወገዙ:: «በልመና» የተሰራ እንዲህ ዓይነቱ ግድብ በታሪክ አለመታየቱ «የወያኔ መንግሰትን» ጅላጅልነት በገሃድ ያወጣ እንደሆነ ጆሮ ላለው ሁሉ ተዳረሰ::

የ2004 ዓ/ምን የመሰለ «የጨኸት ጮማ» ዓመት ደግሞ አልታየም:: እራሱን በማቃጠል አብዮት ያቀጣጠለውን የቱኒስያው ወጣት በመኮረጅ ራሱን «መስዋዕት አደረገ» የተባለውና ኋላ የአዕምሮ ሕመምተኛ  መሆኑን የተረጋገጠውን ወጣት ተጠቅሶ «ፋኖ ተሰማራ» ተዜመ:: አብዮት በማቀጣጠል «ከኛ ወዲያ ላሳር» በሚል መንፈስ  የጨኸት ጥግ ቀረበልን:: የተናፈቀውን አብዮት በተጠበቀው ጊዜ ሳይቀጣጠል ቢቀር ወጣቱ ነዳጅ ተወዶበት እንደሆነ በማለት በዚሁ ሀብት ለታደሉት የዐረብ ሀገራት ማቀጣጠያ ፍለጋ ተሰማራ:: ነዳጁ መገኘቱ  ርግጠኛ መሆን ባይቻልም ፀሎታቸው ይሰምር ዘንድ ራሱን የሚያቃጥል ወጣት እንደላገኙ ግን ድፍን ሃገር ይመሰክራል:: በአክራሪው ዳያስፖራ መንደር ጨኸት መልኩ ይቀይር እንደሆን እንጂ ከቶ አይቆምም:: እናም የሚጮህበትን ሌላ ጮማ «ዜና» ከወደ ጉራ ፋርዳ ደረሰለት:: «አማራው እየተነቀለ ነው» ሲል ዜማውን ቃኘ:: እሰኪበቃው ድረስም አዜመው:: አማራው እስከመቼ ድረስ ይህንን ስቃይ እንደሚታገስ ምፀታዊ ጨኸቱን አስተጋባ:: ለዚህ ሀይል መርህ ጉዳዩ አይደለም:: «ወያኔ ኢትዮጵያን እየከፋፈላት ነው»ብሎ በጮኸበት  አፉ የአማራ «ተነስ» መፈክሩን ካድማስ አድማስ አስተጋባ:: ለሁሉም ጊዜ አለውና ይኸኛውም አለፈ:: ጭር ሲል የማይወደውን የአክራሪው ዳያስፖራ መንደር ግን «መንግሰትን በ 6 ወር እገለብጣለሁ» የሚል «መሲህ» በነፍሱ ደረሰለት:: ስለሆነም ሌላ አዲስ ዜማ ሌላ አዲስ ጨኸት ሆነ:: የቃለ-መጠይቅ መዓት ተዥጎደጎደ::የስትራተጂ ንድፎች ተተነተኑ፤ ገሚሱ የአፈፃፀም መረጃ ዋጋው «እጅግ የከበረ» ስለነበር በጥብቅ ሚስጢር እንደተያዘ ተለፈፈ:: በኢንቨስተርነትና በነፃነት ታጋይነት መሀከል ያለው መስመር እጅግ ከመቅጠኑ የተነሳ ድፍን ሀገር ጉድ ተሰኘ::

የሊዝ አዋጅ መውጣቱንና የሀገሪቱን ለም የእርሻ መሬቶችን ለህንዳውያንና ለመካከለኛው ምስራቅ ባለሃብቶች በኪራይ መሰጠቱ «የ21ኛው ክ/ዘመን ታላቅ ነውር» መሆኑን ተለፈፈ:: ሀገሪቱ በትንሽ በትንሹ ተቆራርሳ ለማለቅ አንድ ሐሙስ ብቻ እንደቀራት ሰለሆነም ይህንን ጉድ ለማየት ዕድሜ የሰጠውን ፈጣሪ ክፉኛ ተማረረበት:: በዚህም ከመንግስተ-ሰማያት

ወደሚያስተሳስር ታላቅ ክንዋኔ ራሱን አሸጋገረ፤ ወደ ዋልድባ ግንባር፡፡ «ዋልደባ ተደፈረ»፤ ተዋህዶ ቤ/ክርስትያን ጉድ ሆነች ተባለ፡፡ በአንዳንድ የትንቢት ተናጋሪዎችም የምፅአት ቀን የመድረሱ ምልክት በመሆኑ ለንስሀ ራሳችንን እንድናዘጋጅ ተነገረን፡፡ በዛሬማ ወንዝ ላይ የሚሰራውን ግድብም ለዚሁ ዓላማ የተዘጋጀ የ«ጥፋት ውሃ» ተብሎ ተነገረለት፡፡ ዘግየት ብሎ ለተከሰተው የአቡኑ «ሞት»ም የዚሁ ድፍረት ውጤት እንደሆነ የቡድኑ «ባህታውያን» ከፈጣሪያቸው እንደተገለጠላቸው ነገሩን፡፡ ቡድኑ እንዲቀጣጠል የሚፈልገው አብዮት በህዝበ-በክርስትያኑ አመፃ ብቻ ግቡን አይመታም፤ ስለሆነም ህዝበ-ሙስሊሙንም መጨመር ነበረበት፡፡ እናም የጨኸቱ አካል ሆነ፡፡ መንግስት አዲስ የእስልምና ሀይማኖት «ኢምፓርት» ማድረጉንና አማኞች በግዳቸው እንዲከተሉት መወሰኑን ተነገረን፡፡ህዝበ-ሙስሊሙ መንግስት ላይ እንዲነሳሳ የተቻላቸውን አደረጉ፤ በማድረግም ላይ ናቸው፡፡

ለዚህ ቡድን በአመቱ መጨረሻ ላይ የተሰማውን የዜና «ጮማ» ያህል ጮቤ የረገጠበት ሁኔታ ግን አጋጥሞት አያወቅም፡፡ ለካ ደስታም ሲበዛ መቋቋም አይቻልም፡፡ በሐዘን ልቡ የተሰበረውን ህዝብ ምን ማለቱ እንደሆነ መገንዘብ እስኪያቅተው ድረስ በደስታ ብዛት ሰከረ፡፡ ሰው ካልተመታ ወይም ካልተከፈለው በስተቀር በዚሁ መጠን ማንባት እንደማይቻለው ለራሳችን መልሶ ነገረን፡፡ ቀጥሎም ከዚህ በኋላ «ማንኛውም ነገር እንደነበረው አይቀጥልም» ተባልን፡፡ ፍርሃታችን ይበዛ ዘንድ የሚቾችና «አልጋ ላይ ሆነው የሚያሟሟቁትን» ቁጥር በየቀኑ እያሻቀበ መሄዱንና በኢትዮጵያ ውስጥ «አውራ ሐጥያተኞች» የሆኑትን አቡን፣ ጠ/ሚኒንትርና ባለሃብት መሞታቸውንና ለኢትዮጵያችን ከሰማይ የተበረከተ «ታላቅ» ስጦታ እንደሆነ በተለመደው የጨኸቱ ቃና ደጋግሞ ነገረን፡፡ ቀጥሎም ገዢው ፓርቲ በስልጣን ሽኩቻ ላይ መጠመዱንና ሀገሪቱ ወደ እርስበርስ ጦርነት ማምራትዋን አይቀሬ እንደሆነ የትንተና ጎርፍ ተዘኀደኀደ፤ትንቢት ተነገረ፡፡ «ሚስኪኗ ሀገር ለመታደግም» የአባይ መዳረሻ ወደሆነችውን ካይሮ በመምዘግዘግ የስደት ላይ መንግስቱ ዕውቅና ቢሰጠው የህዳሴውን ግድብ እንደሚያስቆም ምሎና ተገዝቶ ቃል ገባ፡፡በዚሁም ከራስ ዳሽን ተራራ በገዘፈ ተስፋ ተሞልቶ ወደ ቋሚ መጮኸያ ቦታው እንደተመላሰ ያሰበውን አለመሆኑን ሲረጋገጥ ተስፋ በቆረጠ አሃኔን «ዕድለ-ቢስ ሃገር» ሲል ተዘባበተ፡፡

እላይ በከፊል የተዘረዘሩትን የአክራሪው ዳያስፖራ ተግባራት ዴሞክራሲያዊ ሂደታችንን በጨኸታቸው መጠን ወደ ኋላ እየጎተቱት ነው፡፡ ስህተቱ ያለው «እዚያ ጋር ነው» የሚለውን ስር የሰደደ በሽታ በተቃራኒ ጎራ የተሰለፈውን ሀይል እንዳይለዝብና ለጨኸታቸው የሚሰጠውን ግምት እንዲቀንስ ውይም ጨርሶ እንዲጠፋ ምክንያት ሆነዋል፡፡ ይህ ቡድን የሚከተለውን የትግል ስልት «የትም ፍጭው ዱቄቱን አምጭው» የሚል በመሆኑ ስልጣን ላይ ያለው ፓርቲም ይህንን ተግባር ለመቆጣጠር የሚያስችለው የአሰራርና የህግ ማዕቀፍ ተግባራዊ

ያደርጋል፤ ስለሆነም «ምህዳሩ ጠበበ» ብሎ የሚጮኸውን ቡድን ምህዳሩን ለማጥበብ ራሱ የተጫወተውን ሚና እንደተሰወረበት ይኖራል:: ይህ ሁኔታ በሰዎች ፍላጉትና ሆን ተብሎ የታሰበበት ሁሉ ላይሆን ይችላል:: ስርዓታዊ ችግሮች አብዛኛውን ጊዜ የሚመነጩት በረዥም ጊዜ ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን ከአጭር ጊዜ አንጻር በሚገኙ ጥቅሞች ስለምንለውጣቸው ነው:: አክራሪው ቡድን አቋሙን ባከረረ መጠን በተቃራኒው ጎራ የአቋም መላላት እንዲኖር መጠበቁ አስገራሚ ነው:: ተፈጥሮ በሁሉም መስኮች ራስዋን የምታካክስበት መርህ አላት:: ብዙዎቻችን እንደምንገነዘበው መርሆች ከሰዎች እሳቤና ፍላጎት ውጪ ነው የሚጓዙት:: የሰዎች ዋነኛ ተግባራትም እሴቶቻችንን ከመርሆዎቹ ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው:: የተፈጥሮና ማህበራዊ መርሆዎችን ችላ በማለት ወይም ባለመገንዘብ የምንከውናቸው ተግባራት የተፈለገውን ውጤት አያስገኙም ብቻ ሳይሆን ካሰብነው ተቃራኒ ሆነውም ሊገኙ ይችላሉ:: ከልክ ያለፈ ጥላቻን እዚያ ማዶ ፍቅር እንዲወልድ የሚያስብ ሐይል ሲጀመር ጤንነቱ መመርመር ይገባል:: ምንም ያክል የፖለቲካ ልዩነት ቢኖር በሰው ሞት ላይ የሚጨፍር ሐይል ስለዴሞክራሲ ባህሪያዊ መርሆችን መናገር ይቅርና እንደሰው ቆሞ መሄዱ ሊያፍርበት ይገባል:: በግለሰቦችና በስርዓታት መካከል ያለውን ልዩነት መለየት የተሳነውን ቡድን ስለ ዲሞክራሲ የሚያወራበት ሞራላዊ ብቃት የለውም:: ቡድኑ ዲሞክራሲን«ያዘገያል» ብየ ያልኩት አቅሙ ውስን በመሆኑ በኢትዮጵያችን ላይ የሚፈጥረው ተፅዕኖ ተቋቁመን ወደፊት መገስገስ እንደምንችልና እንዳለብን ስለማምን እንጂ የፀረ-ዴሞክራሲነቱ ጫፍ ወሰን ስላለው አይደለም::

ወደ 1980ዎቹ መለስ ብለን ብንመለከት በመቶዎች የሚቆጠሩ ጋዜጦችና መፅሔቶች ይታተሙ እንደነበር እናስታውሳለን:: ይዘውት ይወጡ የነበረውን የሽብር ልበ-ወለድ ዜና ለመጥፋታቸው ምክንያት እንደሆነ ብዙዎች ይስማሙበታል:: የነባው ፕሬስ ተጨባጭ ሁኔታ ከፕሬስ መርሆዎች ስለተፃረረ ራሳቸው ለፈጠሩት ችግር ስርዓቱ በሰጠው ባህሪያዊ ግበረ-መልስ ተረት ሆነው እንዲቀሩ አድርጓቸዋል:: እሴቶቻችን ማህበራዊ መርሆዎችን በተፃረሩ ቁጥር ቀኑ ይረዝም እንደሆነ እንጂ ዋጋ መክፈላችን ግድ ነው:: በአክራሪ ቡድኑ ዙሪያ እየሆነ ያለውም ይኸው ነው::በሀገር ውስጥ ሆነው በዚህ አክራሪ ቡድን ሳንባ ለመተንፈስ የሚዳዳቸው ወገኖች ሊያውቁት የሚገባ ጉዳይ ቢኖር የራሳቸውና የሀገራችንን የረዥም ጊዜ መሰረታዊ ጥቅሞች እየተፃረሩ እንደሆኑ ነው:: እነሱ ባከረሩ መጠን የሚሰሩበት ምህዳርም መገመት በሚያስቸግር ሁኔታ እንደሚያከርባቸው መገንዘብ አለባቸው::ይህ አባባል ከመንግስት የሚመነጭ ተፅዕኖ ሊሆን ግድ አይደለም:: የህዝቡ ንቃተ-ህሊና መጨመሩና ምክንያታዊነትን የዕውነት ማግኛ ዋናው መንገድ አደርጎ መወሰዱ ውትፍትፉ የተቃውሞ ፖልቲካን የሚንቅበት ሁኔታ ይፈጥራል:: እንዲህ ዓይነቱ ንቃት ከደንቦችና አዋጆች በላይ ተቋሚዎችን እንደሚጎዳ ሊያወቁት ይገባል::

ሌላው የኢ-ስርዓታዊ ችግሮች ሰለባ የሆኑ ሰዎች የሚጠቁበት ምክንያት በውሳኔዎቻቸውና ውሳኔዎቻቸውን በሚያስከትሉዋቸው ውጤቶች መካከል ያለውን መስተጋብር አለመገንዘባቸው ነው። ውሳኔዎቻቸውና የሚያስከትሉት ውጤት በቁጥጥራቸው ስር ያሉ አድርገው ያስባሉ። እውነታው ግን ከዚሁ በእጅጉ የተለየ ነው። ውሳኔዎቻችን እጃችን ላይ ያሉ ቢሆንም የሚያስከትሉት ውጤት ግን በስርዓታዊ በመስተጋብር ነው የሚወሰነው። በዚሁ መሰረት ማንኛ ውም ሰው በሃገሪቱ ህጎች መሰረት ህገ-ወጥ ከተባሉ ቡደኖች ለመስራት መወሰንም አለመወሰንም ይችላል፤ መሳተፉን ከመረጠ በኋላ ግን ስራ ላይ የሚውለው ህጉ እንጂ የሰውየው ፍላጎት አይደለም። አክራሪው ቡድን አልገለጥ ያለው ይህ ይመስለኛል። ፈረንጆቹ እንደሚሉት «ኬኩን በተመሳሳይ መብላትም ማቆየትም» አይቻለውም። ስለሆነም ከዚህ ድርጊቱ የማይመለስ ከሆነ ለመጪው ትውልድ የሚተርፍ ቁምነገር የመስራት አጋጣሚው እንደራቀበት ይኖራል።

ሌላው የአክራሪ ቡድኑ የጎን ውጤት የሆነ በገዢው ፓርቲ ውስጥና በዜጎች መካከል ሊኖር የሚገባውን መተቻቸት ዝቅተኛ እንዲሆን ስለሆነም የመልካም አስተዳደር ጉድልቶቻችንን በጊዜ የማረም ዕድሎቻችንን የሚፈታተን መሆኑ ነው። ትችቶችን ከዋናው አውዳቸው(ኮንቴክስት) በማራቅ የሚተረጉም ሀይል ባለበት ሃገር ከቅንነነት የሚመነጩ ግልፅ ሂሶችን ማቅረብ አስቸጋሪ ያደርጓል። በዚህም የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታችን ፍጥነት ይቀንሷል።

ሁሌም ደጋግመን እንደምንለው ራስን አሰይጥኖ ሌላውን መልዐክ እንዲሆን መጠበቅ ምንጩ ምንም ይሆን ምን ማንንም ተጠቃሚ አያደርግም። አክራሪው ሀይል አፍንጫው ስር ያለውን እውነት ሊጋፈጥ ይገባል። ኢትዮጵያ ውስጥ ለውጥ ለማምጣት ፍላጎቱ ካለው አሁን እየሄደበት ያለውን መንገድ እርግፍ አድረጎ መተው ይኖርበታል። ሃገሪቱ ለልማት በምትተጋበት ሁኔታ ከታሪካዊ ጠላቶችዋ በማበር ጉዞዋን ማሰናከል ታላቅ ክህደት ነው። ማንም ቢሆን ክህግ እንጂ ከህሊና ዳኝነት ማምለጥ አይቻለውም።